# ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ላልዎት ጥያቄዎች የታመኑ መልሶች

**ሜይ 25, 2021**

በካናዳ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አራት (4) የክትባት ዓይነቶች ከመንግሥት ፈቃድ አግኝተዋል፡፡ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ክትባቱን ወስደዋል፡፡ ይህ የማስታወቂያ ጽሑፍ ክትባቱን በሚወጉበት ጊዜ ወደ ሰውነትዎ የሚገባው ምን እንደሆነ ለማወቅ እና በዚህ ረገድ ሊኖርዎት ለሚችሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ማስታወቂያ የተካተቱት መረጃዎች በተመራማሪዎች እና በዶክተሮች የተረጋገጡ ናቸው፡፡



## አለርጂ ቢኖረኝ ክትባቱን ለመወሰድ እችላለሁ ወይ?

አዎን፡፡ የምግብ፣ የመድኃኒትም ሆነ የሌሎች ንጥረ ነገሮች ከፍተኛ አለርጂ ቢኖርዎትም የኮቪድ-19 ክትባት ለመውሰድ ይችላሉ፡፡ የአለርጂ ችግር ያልዎት ከሆነ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ እዚያው የተወጉበት የጤና ማዕከል ምንም ችግር እንደማይኖርዎት ለማረጋገጥ ለ30 ደቂቃ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ አልፎ አልፎ ለሚከሰት ችግር እርዳታ ለመስጠት የጤና ባለሙያዎች ሁልጊዜም በሥፍራው ይገኛሉ፡፡ እንደ polyethylene glycol [PEG] ወይም polysorbate የመሳሰሉት በኮቪድ-19 ክትባት ውስጥ ለሚገኙ ንጥረ ነገሮች አለርጂክ ከሆኑ ወይም የመጀመሪያውን ዶዝ በወሰዱ ጊዜ የአለርጂ ችግር አጋጥምዎት ከነበረ ዶክተርዎን ማነጋገር ይኖርብዎታል፡፡
ከፍተኛ ችግር የሚያመጣ አለርጂ እምብዛም አይከሰትም፡፡



## የጤና ችግር እያለኝ ክትባቱን መውሰድ እችላለሁ ወይ?

እንደ ስኳር በሽታ፣ የደም ብዛት/የደም ግፊት፣ የልብ ሕመም፣ አስም ወይም የደም ማነስ ቢኖርዎትም ክትባቱን መውሰድ ይችላሉ፡፡

የጤና ችግር ካልዎት፣ የበሽታ መከላከያ ሲስተም (immune system) ችግር ካልዎት፣ ኪሞቴራፒ እየወሰዱ ከሆነ አለዚያም የስቴሮይድ መድኃኒት የሚወስዱ ከሆነ ክትባቱን መቼ መውሰድ እንደሚችሉ ለማረጋገጥ የጤና ባለሙያ ወይም ዶክተርዎን ማነጋገር ይኖርብዎታል፡፡



## በርካታ ሰዎች ክትባቱን እስኪወስድ መጠበቅ ይሻለኛ ይሆን?

አይ፡፡ ክትባቱን ለመውሰድ ተራዎት በደረሰ ጊዜ ይውሰዱ፡፡ የኮቪድ-19 ቫይረስ እንዳይዝዎት ይከላከልሎታል፡፡ እስከ ሜይ 25, 2021 ድረስ በዓለም ዙሪያ ከ1 ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦች ክትባቱን ወስደዋል፡፡ ይህንን ወረርሽኝ ለማጥፋት አብዛኛው ሕዝብ ክትባቱን መውሰድ አለበት፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙውን ሕዝብ መከተብ ከተቻለ የማኅበረሰቡን ጤንነትና ደህንነት መጠበቅ ይቻላል፡፡





## ክትባቱ ለምን ያህል ጊዜ ከወረርሽኙ ይከላከልልኛል?

በዚህ ጥናት ላይ የተሰማሩት ተመራማሪዎች ክትባቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚከላከል በርግጥ ለማወቅ ምርምራቸውን እንደቀጠሉ ነው። የክትባቱን የመከላከል ኃይል የሚያጎለበቱ ተጨማሪ ዶዞች ወደፊት መወጋት ያስፈልግዎት ይሆናል።

የኮቪድ-19 ክትባት አንድ ወይም ሁለት ዶዝ መውሰድ ያስፈልጋል። የተወጉት ክትባት ሁለት ዶዝ የሚያስፈልገው ከሆነ ለሁለተኛው ዶዝ እዚያው የተወጉበት ማዕከል ሁለተኛውን ዶዝ ለመውሰድ ተመልሰው እንዲመጡ ቀጠሮ ይሰጥዎታል። የኮቪድ-19 ቫይረስ ከሚያስከትለው በሽታ ወይም ሞት ይበልጡን ለመከላከል የመጀመሪያውን እና የሁለተኛውን ዶዝ መውሰድ ይኖርብዎታል።

አስታውሱ! እንደ ጭንብል (ማስክ) የማደረግ፣ እስከ ሁለት ሜትር ርቀትን የመጠበቅ እና እጅዎትን የመታጠብ የኮቪድ-19 የደህንነት መመሪያዎች ክትባቱን ከወሰዱ በኋላም መጠበቅ እንደሚኖርብዎት አይዘንጉ!

ክትባቶቹ እርስዎን እና ወዳጆችዎን ከኮቪድ-19 በሽታ ይከላከላሉ። ክትባቱን የሚወስዱት ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የበለጡ ሕዝቦች ከወረርሹ ይጠበቃሉ!

**ይህንን መረጃ ጠቃሚ ሆኖ እንደሚያገኙት ተስፋ እናደርጋለን። ለሌሎች ሼር በማድረግ እንዲያዳርሱት እንጠይቆታለን። መልክቱን በቪዲዮ ቀርጸውም ሊያስተላልፉት እንደዚሁም በሌላ ቋንቋ ተርጉመው ማስተላለፍ ይችላሉ።**

**ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ይህንን መረጃ ያዘጋጁትን አካላት እንደ ምንጭ አድርገው መጥቀስ አይርሱ። እነዚህም ውመንስ ኮሌጅ ሆስፒታል (Women's College Hospital)፣ ኦካሲ (OCASI) ፣ ታይቡ የጤና ማዕከል (TAIBU Community Health Centre) እና ሬፉጂ 613 (Refugee 613) ናቸው።**

*ሜይ 25 2021 በተጻፈበት ጊዜ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ*

**በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው መረጃ በሚከተሉት የካናዳ ሐኪሞች ተረጋግጧል - ሜብ ራሺድ MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ረዳት ፕሮፌሰር, ቫኔሳ ሬዲት, MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ሌክቸር, እና አይዛክ አይ. ቦጎች, MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ተባባሪ ፕሮፌሰር**


{REFUGEE}613 TAIBU COMMUNITY HEALTH CENTRE OCASI Ontario Council of Agencies Serving Immigrants WCH WOMEN'S COLLEGE HOSPITAL Healthcare | REVOLUTIONIZED

Funded by: Immigration, Refugees and Citizenship Canada

Financé par : Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada

With contributions from: pchs Serving Diverse Communities, Occupational Health Clinics for Ontario Workers Inc., MCIS Language Solutions